STAY SAFE MN



# ስለ ኮቪድ-19 ክትባቶች በተመለከተ አፈ ታሪኮችን ማረም

ብዙ ሰዎች ስለ አዲሶቹ የኮቪድ-19 ክትባቶች በተመለከተ ጥያቄዎችና ስጋቶች አሏቸው። ይህ የተለመደ ነገር ነው። ይህ ሰነድ ስለ ኮቪድ-19 ክትባቶች የተመለከቱ ዝርዝሮችን ይሰጥዎታል።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባቶችን በማዘጋጀት ረገድ ምንም የደህንነት ደረጃዎች አልተዘለሉም።

የኮቪድ-19 ክትባቶች እንደ ሌሎች ክትባቶች ሁሉ ተመሳሳይ የደህንነት ደረጃዎችና ጥናቶችን አልፈዋል። የህክምና ተመራማሪዎች የአመታት ቀዳሚ የጥናት ልምድ ያላቸውና አብዛኞቹ ከፌደራል መንግስት የተውጣጡ በመሆናቸው ምክንያት ክትባቶቹን በፍጥነት ለማዘጋጀት ችለዋል።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባቶች በተፈቀደው የእድሜ ቡድኖች ውስጥ ላሉ ሁሉም ሰዎች ይሰራሉ።

ሁሉም የኮቪድ-19 ክትባቶች አስተማማኝና የሚሰሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የእድሜ ደረጃዎች፣ ዘርና የዘር ሀረጎች ባሏቸው በአስር ሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ የህክምና ጥናት ተደርጎባቸዋል።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባት የሚሰጠው በነጻ ነው።

የመድን ዋስትና ወይም የስደተኝነት ደረጃዎ ምንም ይሁን ምን ክፍያ አይከፍሉም።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባቶች DNAዎን አይቀይሩም።

የፋይዘር/Pfizer እና ሞደርና/Moderna የኮቪድ-19 ክትባቶች ውስጥ ያለው mRNA (messenger RNA) በፍጹም DNA ወደሚሰራበት የሴሎች ማዕከል የማይገቡ በመሆኑ ምክንያት የአንድን ሰው የዘረመል ስሪት (DNA) መቀየር ወይም ማሻሻል አይችሉም። mRNA ስራውን ከሰራ በኋላ በሰውነታችን ይወገዳል።

## ✔ የጆንሰን ኤንድ ጆንሰን/ Johnson & Johnson የኮቪድ-19 ክትባት በውስጡ የሽል ቲሹ አይይዝም።

ክትባቱ የተሰራው አዴኖቫይረስ ተብሎ የሚጠራ ጉዳት አልባ ቀዝቃዛ ቫይረስ በመጠቀም ነው። ቀዝቃዛ ቫይረሱ በክትባቱ ሰሪ ለአስርት አመታት በተሰበሰቡት የሽል ሴሎች ላይ ያድጋል። ብዙ የእምነት ተቋማት እና የባዮ ስነ ምግባር ተቋማት ሰዎች ሌሎች ክትባቶች በማይገኙ ጊዜ ስነ ምግባርን በተከተለ መልኩ ይህን ክትባ ሊወስዱ እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባቶች ማይክሮ ቺፖችን አይዙም።

አዲሶቹ የኮቪድ-19 ክትባቶች ሰዎችን ለመከታተል ወይም ለመቆጣጠር አላማ ማይክሮ ቺፖችን አይዙም።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባቶች የረጅም ጊዜ ማቆያዎች፣ እንቁላሎች ወይም የአሳማ ስጋ ውጤቶችን አይዙም።

የኮቪድ-19 ክትባቶች፡ ቅባት/ላስቲክ፣ የረጅም ጊዜ ማቆያዎች፣ወይም የአሳማ ስጋ ውጤቶች ወይም መቅኒን ጨምሮ የትኛውንም የእንስሳት ተዋጽኦዎችን አይዙም። ክትባቶቹ በእንቁላል ውስጥ የማያድጉ ከመሆኑም በተጨማሪ የእንቁላል ተዋጽኦዎችን አይይዙም።

## ✔ ነፍሰጡር ሴቶች ክትባቶቹን መውሰድ ይችላሉ።

አሁን ያለን ዳታ የኮቪድ-19 ክትባቶች ጽንሱ ላይ ተጽእኖ አይፈጥሩም ወይም የጽንስ መጨንገፍ አያስከትሉም። የትኛውንም ነፍሰጡር የሆነ ሰው ከትባቱን መውሰድ ስለሚያስገኛቸው ጥቅሞች እና የክትባቱን ስጋቶች ለመረዳት ዶክተሩን እንዲያናግር እናበረታታለን።

## ✔ የኮቪድ-19 ክትባቶች መካንነት አያመጡም።

አንድ ቀን ልጅ መውለድ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የ COVID-19 ክትባትን መውሰድ ይችላሉ። የመራባት ችግሮች ለወንዶች እና ለሴቶች የጎንዮሽ ጉዳት እንደሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ የለም።

## ✔ በኮቪድ-19 ቢያዙም እንኳ ክትባቱን ይውሰዱ።

የሰውነት ኮቪድ-19 ን የመከላከል አቅም ለምን ያክል ጊዜ እንደሚቆይም ሆነ የመከላከል አቅሙ በህመምዎ መጠን ላይ ተመስርቶ ስለመለያየቱ አናውቅም። በተጨማሪም ልዩነቶች በኮቪድ-19 ተይዘው በነበሩ ሰዎች ላይ ምን ያክል ተጽእኖ እንደሚፈጥሩ አናውቅም።

## ✔ በክትባቱ ምክንያት በኮቪድ-19 ሊያዙ አይችሉም።

ክትባቶቹ በውስጣቸው የትኛውንም የኮቪድ-19 ቫይረስን አይዙም።

## ✔ ከክትባት በኋላ የሚመጡ የጎንዮሽ ጉዳቶች የተለመዱ ናቸው።

በ COVID-19 በሽታ ከመታመም ጋር ሲነጻጸር የጎንዮሽ ጉዳቶቹ አነስተኛ ናቸው። መርፌው የተሰጠበት ቦታ ላይ ህመም፣ እብጠት ወይም መቅላት፤ የራስ ምታት መኖር፤ የህመም ስሜት መሰማት፤ የድካም ስሜት፤ እና ዝቅተኛ ትኩሳቶች ሰዎነትዎ ለክትባቱ ምላሽ እየሰጠ እንደሆነ ያመለክታሉ። ብዙውን ጊዜ ከ 1-2 ቀናት ይቆያሉ። የጎንዮች ጉዳቶች ባይኖርብዎትም ምንም ችግር የለውም። እያንዳንዱ ሰው ለክትባቶች የተለያየ ምላሽ ይሰጣል።



## ተጨማሪ ለማወቅ

ስለ COVID-19 ክትባቶች የበለጠ ማወቃችንን ስንቀጥል፣ ይፋ የሚደረጉ አዳዲስ መረጃዎች ወይም ምክረ ሀሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን የህይወት አድን ክትባቶችን ከማግኘት የሚያዘገዩ ምክንያቶች አይደሉም።

## ✔ ከተወሰኑ ግብረ መልሶች በጣም ያልተለመዱ ስጋቶች ይልቅ የክትባቱ ጥቅሞች ያመዝናሉ።

የ Johnson & Johnson ክትባት ላይ የደም መርጋት ችግሮች ወይም ከ mRNA ክትባት (Pfizer ወይም Moderna) በኋላ ማዮካርዳይቲስ/ፔሪካርዳይቲስ የመሳሰሉ ግብረ መልሶች ሪፖርቶች አሉ፣ ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች ያልተለመዱ እና በህክምና የሚድኑ መሆናቸውን ማወቅ አስፈላጊ ነው። የ COVID-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተረጋገጠ ነው። ስለነዚህ ያልተለመዱ ግብረመልሶች እና ህክምናቸው ማወቃችን የክትባት ደህንነት ቁጥጥር ስርአታችን እየሰራ የመሆኑ ማሳያ ነው።

## ✔ ተመራጩ ክትባት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚቀርብልዎ ክትባት ነው።

በ COVID-19 ሳቢያ የሚከሰቱ ከባድ ህመሞችን እና ሞትን ከመከላከል አኳያ ሁሉም የ COVID-19 ክትባቶች በጣም ጥሩ ናቸው። ሁሉም ክትባቶች ዝርያዎቹን በመከላከል ውጤታማ መሆናቸውን አሳይተዋል።

ስለ ኮቪድ-19 ክትባት ተጨማሪ መረጃ ከሚከተሉት ያግኙ
(www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/vaccine/basics.html)

MINNESOTA

mn.gov/vaccine

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 651-201-5000 | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975
አማራጭ ፎርማት ለመጠየቅ health.communications@state.mn.usን ያነጋግሩ። (Amharic)

7/19/2021